# የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ሉኳንዳ ቤት ተገኘ፡፡

# ጀ/ል ፃድቃን በፃፉት  ፅሁፍ ላይ የተሰጠ የግል አስተያየት

<u>በሕጉስ ይካአሉ፣ </u> **07-30-16**

ሰሞኑን ሌ/ጀ ፃድቃን ስለአገራችን ፖሎ ሁኔታና መፍትሄ ብለው ያሰራጩት ፅሑፍ አንብቤ የመፃፍ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በማክበር እንዴት ካንድ ብዙ ልምድ ካለው ሰው የዚህ አይነት ድምዳሜ ይደርሳል ብዬ በመገረም በጠቀስዋቸው ነጥቦችና በሰጡት የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ያለኝ ሐሳብ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

**1ኛ.** የአገራችን ፖሎ ሁኔታና አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን በሚመከት በሰጡት ትንታኔና ድምዳሜ፣

- ስለ ሀገራችን ፖሎ ሁኔታ እናውራ ከተባለ፣ በቅድሚያ የህጎች ሁሉ አውራ ስለሆነው ህገ-መንግስታችንና ፌደራላዊ ስርዓታችን ማንሳት አለብን፡፡ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ለግጭቶች ክፍተት የማይተው ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ወደውና አምነው ያፀደቁት ብሔራዊ ግጭቶችን ለአንዴና ለመጨረሻ የፈታ፣ ክልሎች በቋንቋቸው እንዲተዳደሩ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ እኩል ተጠቃሚነት ያረጋገጠ፣ በመሆኑ እነሆ ሀገራችን ተከታታይ እድገትና ልማት ያስመዘገበች፣ በመላ አለም በፈጣን እድገትዎ የምትታወቅ፣ ከሌሎች በተለየ የተሸለ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ያለበት ሀገር መሆንዋ ሁሉም ተቀብሎ በአርአያነት፣ በጠቀሰበትና አለምን ጉድ ያሰኘ ድህነትን በግማሽ ቀንሳ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አሳኪታ፣ በጣም ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች በራስዋ አቅም በመገንባትዋ እውነትም የተስፋ ደሴት የተባለች ሀገር ለመሆን በቅታለች፡፡ ይህ ሁሉ እድገት የተገኘው ህገ መንግስታችን በተግባር ላይ በመዋሉ እንጂ በፅሑፍ ብቻ የሰፈረ ሰነድ በመሆኑ  አይደለም፡፡

- አንድ ሀገር አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ መግባት አለመግባባቱን የሚመሰክር በጥላቻ ተዘፍቀው እንጥፍጣፊ አቅማቸው አሟጠው በመጠቀምና ትላንት በህዝብ ትግል የተነጠቁት ስልጣን በግርግር ለመመለስ የሚፈልጉ፣ ፅንፈኞች የተናገሩት በመውሰድ የሀገራችን ሁኔታን ሊገልፅ ይችላልን?  ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በየኪክ ቤቱ ጥላቻ በማውራታና ፍላጎትን በመግለፅ የምትፈርስ አገር አይደለችም፡፡ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች እንደ አይን ብሌን የሚያዩት ህገ-መንግስት ለማፍረስ የሚመጣ ኃይል ካለ ለደቂቃም እንደማይታገሱት እየታወቀ፣ ህገ መንግስት ተግባር ላይ አልዋለምና እንሰባሰብ ማለት ኢትዮያዊ ማለት እኛ ነን የሚሉት የትምክት ኃይሎች አጀንዳና ከንቱ ምኞት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

- ስለ አንድ ሀገር ህገ-መንግስት አፈፃፀም ጥንካሬው ተግባር ላይ ዋለ አልዋለም መመዘኛ ነጥብ ፈጣን እድገቱና የተረጋጋ ሠላም አይደለምእንዴ? እስኪ ከአዲስ አበባ በመውጣት ወደ ዓፋር፣ ሱማሌ፣ ትግራይ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ሐረር፣ ደቡብ ሕዝቦች፣ አማራና ኦሮሚያ ገጠሮች ወጣ ይበሉና እንዴት እየተተገበረ እንዳለ መመልከት ይችላሉ፡፡ ከዚህ ውጪ በስሜት ብቻ ህገ-ምነግስቱ ተግባር ላይ እየዋለ አይደልም ማለት የሌለ ችግር መፍጠር እንጂ ችግር ፈቺ ሃሳብ ሊሆን አይችልም፡፡

  - በመላ አገራችን ባለፉት 10 ዓመታት ተከታታይ ባለ ሁለት አሃዝ እድገት የተመዘገበበት በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ደረጃ ፈጣን እድገት ያስመዘገበ መንግስትና ሀገር ያለ ልማታዊ ዲሞክራሲ መንገድና አመራር እንዴት ይህ ሁሉ ልማት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡ በጣም በርካታ ኢንቨስተሮች ተመራጭ አገር ብለው የመረጧት፣ በርካታ ሜጋ ፕሮጀክቶችን፣ የባቡር፣ የህዳሴ ግድብ የስኳር…ወዘተ በራስዋ ወጪ የምትገነባ ሀገር፣ በምን መለኪያ ነው መስቀለኛና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች ብለው ስሜታዊ ግምገማ ያስቀመጡት? ምናልበት ሰምተው ሃቁን እየደበቁ ሁነው ነው እንጂ ፈረንጆች አንድ ሌላ ሀገር እየፈጠራችሁ ነው የሚመስለው፤ ይህ ሁሉ እድገት ገንዘብ ከየት እያመጣችሁ ነው እስከ ማለት የደረሰ የሚያስደምም ልማት በተግባር እያዩ ጀነራሉ እንዴት በኃይልና በጉልበት እያስፈራራ ነው እየገዛ ያለው ወደሚል ጭፍን ሐሳብና ድምዳሜ መድረስ የሚቻለው፡፡

- በተሃድሶ መስመርና በሀገራችን ህዳሴ ሰነድ እንደተቀመጠው በትክክለኛው አቅጣጫ ተመርታ በ 40 እና 50 ዓመታት ጊዜ ውስጥ እነ ኮርያ በተግባር ያረጋገጡትና ከበለፀጉት አገሮች ተርታ መሰለፍ የሚቻለው የኢኮኖሚ ለውጥና ቀጣይነት ያለው እድገት በየምዕራፍ፣ እንዲረጋገጥ ልማታዊ መንግስት ቀጣይነት የማረጋገጥ፣ የገበያ ጉድለቱ በተመረጠ አኳሃን ጣልቃ እየገባ በማስተካከል፣ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖሎቲካል ኢኮኖሚ በቀጣይነት በመታገል፣ የኢኮኖሚ ለውጥና የቴክኖሎጂ ብሎም የመሰረተ ልማት ዕድገት በማምጣት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ የውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት በብዛት እንዲፈጠሩና እንዲያድጉ፣ ብሎም የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖር፣ የሰው የመኖር የእድሜ ጣሪያ ከ 45 – 67 ከፍ እንዲል ያደረገ፣ ከ 30 ባላይ ዩኒቨርስቲዎች የሰራ ፌደራል መንግስት በየትኛው መመዘኛ ነው ጣልቃ መግባቱን የሚቃወሙት፡፡ ትላልቅ የአሜሪካ ኩባንያዎች በነበረው ኢኮኖሚያዊ ችግር ምክንያት ሲከስሩ፣ የአሜሪካ መንግስት የገንዘብ ድጎማ እያደረገ ህልውናቸውን አልጠበቀም እንዴ? ይህን እውነታ

ከኢህአዴግ ተምረናል ባይሉም እነ ኦባማ ተጠቅመውበታልና ጀነራሉ ሰከን ብለው ቢፅፉት ኖሮ የልማታዊ ዲሞክራሲ መንገድ ውጤታማነቱ በታያቸወ ነበር፡፡

- በሌላ በኩልም ሀገራችን ህዝቦች ተሳትፎ ባይታከልበትና ድህነትን የሚቀርፍ ትክክለኛ ፖሊሲ ለዚህ ቁርጠኛ፣ የሆነ አመራር ባይኖር የተመዘገበው እድገት እንዴት ሊገኝ ይችላል፡፡ ለነገሩ ኢህአዲግ እንደ ፖርቲ ሙስናና ብልሹ አሰራር የሚጠየፍ፣ በቀጣይነት የሚታገል ድርጅት መሆኑ፣ ከተነሳለት ዓላማ አንፃር እየመዘነ በየጊዜው ከራይ ሰብሳቢነት እየታገለ ከእያንዳንዱ መድረክ፣ በቂ ትምህርት የሚወስድ በመሆኑ ከህዝብ ጋር ተመካክሮ የሚታዩትን ችግሮች የሚፈታ ድርጅት በመሆኑ ማንም ሳይነግረው የመልካም አስተዳደር፣ እጥረትና የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ ራሱ ያስቀመጠው ሀቅ ነውና ችግሩ ሌላ አካል የነገረው ሳይሆን ራሱ ገምግሞ ጊዜ ሳይሰጥ በቁርጠኝነት እንደሚታገለው በማረጋገጡ ሁኔታው በህዝብ ተሳትፎ ጊዜ ሳይሰጠው በሚደረግ ትግል የሚፈታ እንጂ አደገኛና አሳሳቢ የሚሆንበት ሁኔታ አይፈጠርም፡፡

- ሁላችንም እንደምናውቀው የኢፌዲሪ መከላከያ ኃይልም ሆነ ሌሎች የፀጥታ አካላት በጠንካራ ህዝባዊ ወገንተኝነታቸው የሚመሰገን ታሪክ ያላቸው፣ መስዋእት እየከፈለ አገር የሚጠብቅ በትእግስት ነገሮችን የሚከታተል የሚሰጠው ግዳጅ በእውቀት እና ብቃት ብቃት የሚፈፅም ከአገራችን አልፎ በጎረቤት አገሮች ሰላም ያሰፈነ ሰራዊት መሆኑን አለም የመሰከረለት እንዴት እንዲህ አይነት ሠራዊት በክልል ጉዳዮች ላይ ጣልቃ እየገባ ያስፈራራ ነው ይባላል፡፡ ይህን ውንጀላ እርስዎ ጠቅላይ ኤ/ሹም እያሉ አልነበረምና አሁን ጀመረ እያሉን ነው፡፡ እውነት ይህ ከሆነ ሐሳብዎ ምን ፈልገው እንደፃፉት ያሳብቅብዎታል፡፡

**2 ኛ.** ከኦነግ ጋር የነበረ የግጭት አፈታት በሚመለከት፣

- ከደርግ መንግስት መውደቅ በኋላ በነበረ የሽግግር መንግስት፣ ኦነግ እንደሌሎች የታጠቁ ፀረ ደርግ ኃይሎች በሽግግር መንግስት አስተዋፅኦ እንዲኖረው ታስቦ በስልጣን ክፍፍሉም ከአምስት የበለጠ የሚኒስትርነት ቦታ እንዲያገኝ ተደርጎ በእጃቸው የነበረ የታጠቀ ኃይል የተበተነው የደርግ ሠራዊትን ይጨምራል፣ በካምፕ እንዲሰፍርና አስፈላጊው ምግብ፣ ህክምና፣ መጠለያ እንዲቀርብላቸው ተደርጎ

በሰላም እንዲኖሩ የኢህአዴግ ሠራዊት የሽግግር መንግስት ሰራዊት ሁኖ እንዲቀጥል ተደርጎ እያለ፣ በዚህ ጊዜ የኦነግ ስራ ምን ይመስል ነበር፣ መመልከቱ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

- በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ በማስቆም መዝረፍ፣ መግደል፣ ከየቤቱ ጨለማን ተገን አድርጎ በየጫካው ሰው መግደል ይባስ ብሎም በበደኖ፣ በገለምሶ፣ በወለጋ፣ በሐረርጌ በጣም በርካታ ሰው በመጨፍጨፍ ገደል ውስጥ የከተተ፣ ከደርግ ባልተናነሰ ህዝብን የጨፈጨፈ፣ ድርጅት በምን መለኪያ ነው ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችለው፡፡

- በተለያዩ ካምፖች ሰፍሮ የነበረው ወደ 10,000 የሚጠጋ የኦነግ ታጣቂ በኦነግ አመራር ውሳኔ እኮ ነው በሽግግር መንግስት ላይ ጦርነት ያወጀውና ቻርተሩን ረግጦ የወጣው፡፡ ለገደላቸው ንፁሐን በፓርላማ እንደሚያስጠይቀው አውቆ ነውኮ፣ ጫካ የገባው፡፡ ድሮስ ኦነግ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሚደግፈው፣ ህዝብ ይኖራል ተብሎ ነው እንጂ ኦነግ ከእድሜው ጋር የሚመጣጠን ፀረ ደርግ ትግል አድርጎ ያውቃል እንዴ?
- ኦነግ በረሀ ነበርኩ ባለባቸው ጊዜያት አመራሮች ጀርመንና አውሮፖ ሱፐር ማርኬት በመክፈት መነገድ፣ ከወለጋ ቀርከሃ ወደ ሱዳን ማመላለስና መነገድ ስራቸው እንደነበር ድፍን የኦሮሞ ህዝብ የሚያውቀው ነገር ነው፡፡ በያዛው የህዝብ አላማ መላ ህዝቡን አንቀሳቅሶ ልማት፣ ሰላም የፈጠረው ኢህዴድ/ኢህአዴግ) እንጂ ኦነግ መቼ ሆነ፡፡ የአሸባሪነት ሥራ እንደ አላማ በመያዝ የተለያዩ የሽብር ድርጊቶች በመፈፀም ብዙ ሰላማውያን ሰዎች የገደለው፣ ኦነግ በምን ሒሳብ ነው ለሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሚዛን ጠባቂ የሚሆነው በእውነቱ ጀነራሉ ስለ ኦነግ ግጭት አፈታት የፃፉት ፅሁፍ ቢተኩስብህም እንዳትተኩስ፣ ህዝብ አላማቸውን አውቆ እስኪታገሳቸው ትእግስት እናድርግ፣ መስዋዕትነት እንክፈል፣ ተብሎ ለተከፈለው መስዋእትነትና አስተዋይነት የካደ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የተፃፈ ይመስለኛል፡፡

- በ 1997 ምርጫ ጊዜም አንዳንድ ከሀዲዎች በጠራራ ፀሐይ በአደባባይ እኛ ፀረ ደርግ የታገልነው በስህተት ነበርና ይቅርታ ይደረግልን ብለው ትምክህተኞች ጉያ ሲወሸቁ ታዝበናል፣የቅርብ ትዝታችንም ነው፡፡

- በዚህ ወቅትም ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የ 1997 እድል ዳግመኛ እንደማይፈጠር በመገምገም ልማታዊ መንግስታችን የፀጥታ አካላትን ስም ለማጥፋት ከውጭ ኃይሎች ጋር በመሆን ከፍተኛ ርብርብ እያረጉ በሚገኙበት ጊዜ የተፃፈ በመሆኑ ከዛ፣ የተለያ እውነታና ትርጉም የሌለው መሆኑን ያነበበው ሰው ሁሉ ይስማማበታል ብዬ እገምታለሁ፡፡

- ሌላው ሶስተኛ ነጥቤ ስገባ ስለአገራችን ፖሎ ምህዳር መጥበብ የሰጡት አስተያየት ነው፡፡ እውን በአገራችን ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች አብዛኞቹ በጥላቻና በስሜት የተመሰረቱ እንጂ ግልፅ ፖለቲካዊ ፕሮግራም ይዘው የተነሱ አይደሉም? በሁሉም ምርጫዎች ለህዝብ የሚጠቅም አንዳችም ፕሮግራም ሳይዙ እንዴት ተብሎ ነው ተቃዋሚዎች ህዝብ ሊመርጣቸው የሚችሉ፣ በሁሉም ምርጫዎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጊዜ ተሰጥቷቸው ከስድብና አሉባልታ ውጭ የሚገልፁት ፕሮግራምና አላማ አጥተው የአየር ጊዜውን ሳይጠቀሙበት የባከነ ሰዓት እንደነበረ እንዴት አላወቁም፡፡ ይህ በሆነበት የምን ምህዳር መጥበብ ነው፡፡ በ 1997 ያገኙት ድምፅም ኮ አስበው፣ አቅደው ሰርተው ፕሮግራማቸውን አስተዋውቀው ያገኙት ድምፅ ሳይሆን፣ ህዝቡ ኢህአዴግን ለማንቂያ የሰጣቸው ድምፅ ነው፡፡ ይህን ተቃዋሚዎች ራሳቸው የተቀበሉት ሃቅ ነው፡፡

- እንዴት ተደርጎ ነው ጀነራሉ ተቃዋሚዎች ያገኙት ጠቅላላ ድምፅ አላውቀውም እያሉ ለኢህአዲግ ህዝብ የሰጠውን ድምፅ ቆጣሪ የሆኑት? በምንስ ተሰልቶ ነው የፖለቲካ ምህዳር ጠበበ ኢህአዴግ እያስፈራራ ነው ተብሎ በግምት ውንጀላ ውስጥ የገቡት? ይህ ቁርጦ ቀጥልና የተሳሳተ፣ ተጨባጭ ሁኔታ የማይገልጽ ኢህአዲግ ህዝቡን በፀጥታ አካሉ እያስፈራራ እየተመረጡ ነው፣ ህዝቡ ምንም አያውቅም ብለው መፈረጃ ከዚህ በላይ ህዝብን መናቅና የሚጠቅመውን አያውቅም ማለት ከለየለት የትምክህተኞች አነጋገር በምን ይለያል ?

❖ ወደመጨረሻ ነጥቤ ስመጣ፣ ከአንዳንድ የትግርኛ ተናጋሪ ጓደኞቼ ጋር ስንጫወት፣ በፀጥታ አካሉ ያለን ውክልና ወይም የትግርኛ ተናጋሪው ቁጥር መቀነስ ያሳስበናል ብለውኛልና፣ ይህ የሚያሳስብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንስ መጨነቅ ያለብን ስርዓቱ አደጋ ላይ ነውና ከፀረ ዲሞክራሲ ወገኖች ጋር ሰልፋችሁን አታስምሩ ብዬ ምክር ሰጠሁ ያሉት፣ በእውነት እስዎ ስለአገር ጉዳይ ተጨንቀው ወይስ ስለ ግል ጉዳይዎ ተጨንቀው፤ አሁንም ስልጣን ላይ ወደ ነበሩበት ጊዜ ልመልስዎና ህገ-መንግስታችን የመከላከያ ሰራዊት የብሔር ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች ሚዛናዊ ተዋፅኦ ያካተተ ይሆናል ብሎ ባስቀመጠው መሠረት፣ ሰፊ ልምድ የነበረው የህወሐት ሠራዊት ሶስትና ሁለት ደረጃ ወርዶ እንዲቀመጥ ሲነገረው፣ አብዛኛው ሠራዊት በፀጋ የተቀበለው፣ ይች ሀገር የሁላችን በመሆንዋ በትጥቅ ትግል ከተከፈለው መስዋእት አይበልጥልም ብሎ አይደለምን?

❖ እንዲያውም በተጨባጭ ሰራዊታችን ባለፉት 10 ዓመታት አቅሙን ለማሳደግ በተደረገው ከፍተኛ ርብርብ ከ10 በላይ ኮሌጆች ተከፍተው በርካታ የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት እያንዳንዱ ስራ በእውቀትና በላቀ ብቃት እየተሰራ የሰራዊቱ ስብጥርም ከማንኛውም ጊዜ በላይ መልክ እየያዘ ሕብረ ብሔራዊነታችን የጥንካሬዎች ምንጭ ሁኖ በተግባርም የሀገራችን ተምሳሌትና ጠንካራ ሠራዊት መፍጠር ተችሏል፡፡ ተቋማችን የእውቀትና የምርምር ቦታ በመሆኑ መላ ህዝባችን በተደሰተበት ከምን የመጣ ወንጀላና ስም ማጥፋት ነው፡፡ ለዚህም ነው የት ይደርሳል ያልነው ጥ ያሰባለን፡፡

- በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በተመለከተ ያነሱት ነጥብም በጥናት ያልተደገፈ ሐሳብ፣ ነው፡፡ ትግራይ ክልል የነበሩ የተማሩና ሃብት ያፈሩ የትግራይ ተወላጆች ወደ አዲስ አበባ እየጎረፉ ነው ብለውናል፣ በቂ ሃብት አፍርተው በቂ እውቀት ትግራይ ውስጥ ካከማቹ ወደ ተለያየ ቦታ ሄዶ መስራት ምኑላይ ነው ጥፋቱ፤ ሰፊ ገበያ የሚያገኙበት ምርታቸው በበለጠ የሚሸጥበት ቦታ አዲስ አበባም ሆነ ሌላ ክልል መምረጣቸው ዜግነታዊ መብታቸውን መጠቀማቸው ያረጋግጥ እንደሆነ እንጂ በምን ስሌት ነው የትግራይ ሁኔታ ስላልተመቻቸው ተብሎ የሚፈረጅ፤ አንዳንድ መደዴ ፀሐፊዎች ከመሬት ተነስተው በጥላቻ የሚፅፉትና ገንዘብ ስላገኙ ሁሉንም የሚያውቁ እየመሰላቸው የሚፅፉትን እንደ መነሻ ወስደው ከሆነ ትልቅ ኃላፊነት የጎደለው በጥናት ያልተደገፈ በግልብ ስሜት የተፃፈ ይመስለኛል፡፡ በትክክል ከመቆርቆር የሚነሳ ሐሳብ ቢሆን ዝርዝር ጥናት ተደርጎ በማስረጃ በቀረበ ነበር፣ እከሌ ነገረኝ ብሎ መፃፍ ግን ከተራ ውንጀላ የማያልፍ ሐሳብ ሆኖ አግኝተዋለሁ፡፡

- በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን የተስፋ ደሴት (Iceland of Hope) ተብላ የምትጠራበት ያለምንም የተፈጥሮ ሃብት በጣም ብዙ ሜጋ ፕሮጀክቶች በራስዋ አቅም መስራት የቻለች፣ ድህነትን ከነበረበት በግማሽ የቀነሰች፣ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ያሳካች፣ መፃኢና ብሩህ የሆነች አገር ተብሎ በአለም የተመሰከረላት፣ ማልዶ (ቀድሞ) የተነሳ ነው የሚመራት የምተባል ኤርትራ በስተቀር ሁሉም ይህ ሀቅ በምሳሌነት በሚጠቀስበት ጊዜ አገራችን በችግር ላይ ትገኛለች ብሎ መፃፍ ለዛውም ከፍተኛ የፓለቲካ ሰው ከነበረ ሰው፣ እንዲህ አይነት በጥናት ያልተደገፈ ስሜታዊ ጽሑፍ መፃፍ እውነትም ሰው የሚውለውን ይመስላል ያስብላል፡፡

- ትላንት በትግላችን ያሸነፍናቸው ደመኛ ጠላቶቻችን ከያሉበት ተጠራርተው ህዝቡን ለማናቆር ደፋ ቀና እያሉ እጅግ ዘረኛ የፖለቲካ ዘመቻ በሚያካሂዱበት ጊዜ መንግስትና ህዝብ ኪራይ ሰብሳቢነትን በቁርጠኝነት ለመታገል በተነሱበት ጊዜ ምንም ተጨባጭ ማስረጃ ሳይቀርብ የሰራዊቱን እና የመንግስትን ስም ማጥፋት በጥቃቅን ፍፃሜዎች ወደ ተሳሳተ ፖሎ ድምዳሜ መድረስ እውነትም “ የት ይደርሳል የተባለው ጥጃ ሉኳንዳ ቤት ተገኘ ” እንድንል አድርጎኛል፡፡

ቸር እንሰንብት

ሐጎስ ይከአሎ